የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
Ethiopische Orthodoxe Tewahido Kerk
በኔዘርላንድ ደብረ መዊዕ ቅዱስ ገብርኤል ቤ/ክ
Debre Mewi Heilige Gabriel Kerk in Nederland

ቀን፤ ነሀሴ 5 ቀን 1995 ዓ.ም
Date: August 10 2003

ለኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክርስቲያን ምዕመናን በሆላንድ

ጉዳዩ፡- <u>የሰበካ ጉባኤ አባልነት ምዝገባና ክፍያ</u>

በሆላንድ የምትገኘዋ የኢ.ኦ.ተ. ቤተክርስቲያን እ.አ.አ. ከ1992 ዓ.ም ከተቋቋመችበት ጊዜ ጀምሮ ችሩ አም ላካችን ልዑል እግዚአብሔር በፈቀደው መሰረት ሐዋሪያዊ ግዴታዋን ስትወጣ ቆይታ፡ ሥርአተ ቤ/ክርቲያንና ደንብ በሚፈቅደው መሰረት በቅዱስ ሲኖዶስ ጸድቆ በወጣውና የቤተ ክርስቲያናችን መተዳደሪያና የአደረጃ ጀት መመሪያ በሆነው ቃለ ዓዋዲ በሚያዘው መሰረት ለመጀመሪያ ጊዜ በአጥቢያ ሰበካ ጉባኤ ደረጃ ለመደራጀት ህዳር 1 ቀን 1995 ዓ.ም (November 10/2002) የሰበካ ጉባኤ አመራር አባላት መመረጡ የሚታወስ ነው ፡፡

ይህ ኮሚቴ ከተመረጠ ወዲህ አበይትና አጣዳፊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሲነጋገርና ሲመካከር ቆይቶ ነሀሴ 4 ቀን 1995 ዓ.ም. (August 10 2003) ባደረገው የሰበካ ጉባዔው አመራር አባላት መደበኛ ስብሰባ ላይ የኢ.ኦ.ተ ቤ/ክ በሆላንድ የደ/መ/ቅ/ገ/. ቤ/ክርስቲያን ምእመናን የሰበካው ጉባኤ የአባልነት መመዝገቢያ ቅጽን ይዘት፡ወርሀዊና የአገልግሎት ክፍያን በሚመለከትና እንደዚሁም በአባላት መብትና ግዴታ ዙሪያ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ከዚህ በታች ያሉትን ውሳኔዎች አስተላልፏል ፡፡

1. ያባላት መመዝገቢያ ቅጽ (ፎርም) ከመስከረም እስከ የካቲት ወር 1996 ዓ.ም. መጨረሻ ባለው ጊዜ ውስጥ ምእመናኑ በየአቅራቢያው ካሉት የሮተርዳም፡ የዴንሃግና አምስተርዳም ሰንበት ት/ቤቶች በመውሰድ ወይም በቅዳሴ አገልግሎቶች ሰዓት እየተሰጠ ፈቃደኛ የሆነ ሁሉ እንዲመዘገብ።
2. የሰበካ ጉባኤው አባል ሆኖ የተመዘገበ ምዕመን ወይም ቤተሰብ (እድሜአቸው እስከ 18 ዓመት ድርስ ያሉትን ሁሉ ይጨምራል) በየወሩ 5.00 (አምስት) ኤውሮ እንዲከፍሉ፡
3. እድሜአቸው ከ 18 ዓመት በላይ የሆናቸው ከቤተሰብ ጋርም ሆነ ለብቻቸው እየኖሩ የራሳቸው ሥራና የገቢ ምንጭ ያላቸው ለብቻቸው እንዲመዘገቡና በየወሩ 5.00 (አምስት) ኤውሮ እንዲከፍሉ፡ ወስኗል።

   በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያናችን ያለባትን የተለያዩ ወጪዎች ለመሸፈን ይረዳ ዘንድ ምእመናት ለሚገኙት ግልጋሎት ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ውስጥ የተጠቀሰውን እንዲከፍሉ ተወስኗል ።

<u>ለአገልግት የሚከፈል</u>

| ተ.ቁ | የአገልግሎት አይነት | የተመዘገበ አባል | ያልተመዘገበ ምዕመን |
|---|---|---|---|
| 1 | ለክርስትና | 10.00 | 50.00 |
| 2 | ለተክሊል ጋብቻ | 50.00 | 150.00 |
| 3 | ለሙታን ፍትሃት ማስፈጸሚያ | 50.00 | 150.00 |
| 4 | ለሙታን ጸሎትና ስም ማስጠሪያ | 10.00 | 25.00 |

<u>ማስታወሻ፤</u>
የቤተ ክርስቲያናችንን ግልጋሎት ለሚሹ በሆላንድ ላሉ የኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክርስቲያን ተከታዮችን ሁሉ በአባልነት ለመመዝገብ ይረዳን ዘንድ በአካባቢዎ የሚገኙ ወይንም የሚያውቋቸው የቤተክርስቲያናችን አማኞች ካሉ እርስዎም ይህንን ቅጽ በመውሰድ ሞልተው እንዲመልሱልን በማድረግ ወይም ከሶስቱ ወደ አንዱ ሰንበት ት/ቤ ብቅ ብለው ቅፁን እንዲሞሉ በመንገር የርስዎን ትብብር ቤተ ክርስቲያንዎ ትጠይቃለች፡፡

እግዚአብሔር ቤተክርስቲያናችንና መሰባሰባችንን ይባርክ፡ አሜን።
የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ በሆላንድ የደብረ መዊዕ ቅ/ገብርኤል ቤ/ክ መንፈሳዊ ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት

Adres:- Heilige Gabriel EOTK in Nederland
Postbus 13001
2501 EA DENHAAG
Tel:- 0645202205
0645434175
0626710595
Postbank Gironummers:- 9520951 (Parochie=Sebeka) and 2958075 (Gebouwcomité)